# ***<u>ወቅቱ ተግባራዊ ምላሽ የሚሰጥበት ነው!!!</u>***

## ***<u>ከተለያዩ የኢትዮጵያ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች የተሰጠ የጋራ መግለጫ</u>***

በሥልጣን ላይ ያለው የወያኔ መንግስት ሀገሪቷን ከተቆጣጠረበት እ.ኤ.አ 1991 ዓ.ም ጀምሮ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያን፤ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ፤ ቁልቁል እየንተታት ይገኛል።

ህዝብን ሳይጠይቅ፤ ከህዝብ ሳይመክር፤ ኤርትራን በማስገንጠል ግንባር ቀደም ሚና በመጫወት፤ አንድ ቤተሰብ የሆኑትን ህዝቦች ካለያየ በህዋላ፤ ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ሀገር አድርጓታል። ያለ ህዝብ ፍላጎት፤ አዲስ አበባና አስመራ ላይ የነገሱት መለስ ዜናዊና ኢሳያስ አፍወርቂ፤ በጋራ የዘረፏቸውን በመካፈል ላይ ተጣልተው፤ ከሁለቱም ወገን ወደ መቶ ሺህ የሚጠጋ ሰው በጦር ሜዳ እንዲማገድ ሆኗል። ጦርነቱን 'በድል' ካጠናቀቅን በህዋላ፤ በዓለም ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ መልኩ፤ አልጀርስ ላይ ስምምነት በመፈረም 'ድሉ' እንዲቀለበስ ተደርጓል።

በምስራቁ የሀገራችን ክፍል፤ በማያገባውና በማይመለከተው ጉዳይ፤ የቡሽ አስተዳደርን ድጋፍ ለማግኘት ሲል ብቻ፤ ጦር ሰብቆ ሰራዊት ልኮ፤ ሶማልያን ወረረ። በሁለት ሳምንት ውስጥ በድል እንወጣለን ተብሎ እንዳልተዘፈነና ከበሮ እንዳልተደለቀ፤ ወረራንና ጣልቃ ገብነትን በተቃወሙ የሶማልያ ወጣቶች ተገዶ በሽንፈት አቀርቅሮ በመውጣት ላይ ይገኛል።

በምዕራቡ 'ግንባር' ደግሞ፤ አሁንም በሥልጣን ላይ ለመቆየት በሚደረግ ጊዜያዊ ጥቅም፤ የሀገር ድንበር፤ ከህዝብ ሳይመክር፤ ለሱዳን እየሸነሸነ ሰጠ።

አብዮታዊ-ዲሞክራሲ በሚል የተዳቀለ ፕሮግራም፤ የአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ አስተዳደር መሰረተ። በዚህ ግራ የተጋባ ፕሮግራም መሰረት፤ መድበለ ፓርቲ የሚፈቀደው፤ ሲቪክ ማህበራት እንዲንቀሳቀሱ የሚፈቀድላቸው፤ ነፃ ጋዜጦች የሚታተሙትና የሚሰራጩት፤ የወያኔ ደጋፊና ጥገኛ እስከሆኑ ድረስ ብቻ ነው። ከዝያ ውጭ፤ ሀሳብን መግለፅ፤ መቃወም፤ መደራጀት፤ የመሳሰሉት መሰረታዊ የሰው ልጆች ተፈጥሯዊ መብቶች የተከለከሉ ናቸው። የመንግስት መዋቅር በፓርቲው ቁጥጥር ስር ወድቀው፤ የወያኔ ግፍ ማስፈፀሚያ ተቋማት ሆኑ። ምርጫ ቦርድ የውሸት ሆነ፤ ፍርድ ቤቶች ከአቶ መለስ ትዕዛዝ የሚሰጣቸው አሻንጉሊት ሆኑ፤ የመንግስት መገናኛ ብዙሃን፤ የወያኔ አፈ-ቀላጤና ፕሮፓጋንዳ መንዣ ሆኑ፤ የፀጥታ ሀይሎች፤ ፖሊስና ጦር ሰራዊቱ፤ ለአቶ መለስና ለወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣናት አቤት ወዴት የሚሉ፤ ተላላኪዎች ሆኑ። የከተማና የገጠር መሬት በወያኔ ቁጥጥር ሲሆኑ፤ የነፃ-ገበያ ፖሊሲ ከወረቀት ያላለፈ ሆነ። ከፓርቲ ኩባንያዎችና ቅርቦቻቸው በስተቀር ነግዶ ማትረፍ የማይሞከር ሆነ። ገበሬው አርሶ መብለት፤ ሰራተኛው ሰርቶ ማደር የሩቅ ተስፋ ብቻ ሆኑበት።

በዚህም ምክንያት፤ በሃገራችን ድህነት ተባባሰ። በአንፃራዊ መልኩ የተሻለ ምርት ይታይባቸው የነበሩ የደቡብና ምዕራብ ሀገራችን ክፍሎች ጭምር በድርቅ ይጠቁ ጀመር። የሥራ አጥ ቁጥር ተበራከተ፤ ዋጋ ሽቅብ ተስፈነጠረ።

ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብም እምቢኝ አልገዛም ማለቱን አላቋረጠም። በገጠር በከተማ፤ በሀገር ውስጥና ከሃገር ውጭ በግልና በቡድን ትግሉን ተያያዘው። ገዡው ሀይል በግፍ ማሳደዱን፤ ማፈኑን፤ማሰሩንና፤ መግደሉን አፋፋመው። በአኝዋክና በሶማሊያና በኦሮሞ ብሔረሰቦች ላይ የተወሰደው ጅምላ ጭፍጭፋ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጋለጡ፤ ተወገዙም። በጋምቤላ፤ በቴፒ፤ በወሊጋ፤ በአርሲ፤ በሃረር፤ በጎጃም፤ በወሎ፤ በጎንደር፤ በኦጋዴን፤ በአዲስ አበባ፤ በአጠቃላይ፤ በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች፤ ህዝቡ ላይ የግፍ ግፍ ተፈፀመ። በኦሮሞው፤ በትግራዩ፤ በጉራጌው፤ በአማራው፤ በወላይታው፤ በሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችና ቋንቋ ተናጋሪዎች ላይ ጥቃት ተሰነዘረ። እስላምነ ክርስትያኑ በአንድ ላይና በተናጠለ ተዘመተባቸው። ወጣቱ፤ አዛውንቱ፤ ህፃናት፤ ሴቶች፤ ወንዶች፤ የወያኔ ሰለባ ሆኑ። በቅርቡ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር በሆኑት ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ፤ በታዋቂው አርቲስት ወጣት ቴድሮስ ካሳሁን / ቴዲ አፍሮ/ እና በሌሎች የነፃነትና የፍትህ ተሚጋቾችና ታጋዮች የተወሰደው የእስር እርምጃ፤ የወያኔን ግፈኛ አገዛዝ መጠዙን ያመለክታል።

ወያኔ ይህንን ግፍ የሚያደርገዉ "ከልካይ የለኝም፣ ህዝብ ተከፋፍሏል፤ ፈርታል፤ ደካማ ነዉ» በሚል የማን አለብኝነት እብሪት ተወጥሮ ነው።

ስለሆነም አገር ከመጥፋቷ በፊት ወደ ገደል ዉስጥ እየወሰደን ያለዉን የጥፋት ባቡር ማስቆም ታሪካዊ የዜግነት ግዴታችን ነዉ። የኢትዮጵያዉያን አንድነትና መተባበርም የግድ ነዉ። ስለሆነም እኛ ስማችን ከታች የተዘረዘረዉ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራት የሚከተሉትን አቋሞች በጋራ አሳልፈናል፡

1. ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ለዲሞክራሲ ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር፣ አቶ በቀለ ጂራታ የኦሮሞ ፌደራሊስት ደሞክራሲያዊ ንቅናቄ ዋና ጸሃፊ ፣ አቶ አበራ የማነ አብ የቀድሞ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኅያሎች ቅንጅት ተወካይ፣ ታላቁ የኪነት ሰዉ ወጣት ቴዎድርስ ካሳሁን እንዲሁም በፖለቲካ አቋማቸዉ የታሰሩ፣ በብዙ ስማቸዉን የማናዉቃቸዉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች በየክልሉ ያሉ እሥር ቤቶችን አጣበዋል። በቅርቡም የመኢአድ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ሃላፊ የሆኑት ወ/ሮ መሰበወርቅ ታስረዉ በዋስ መለቀቃቸዉ የሚታወስ ነዉ። ስለሆነም ሕወሃት እንዳሻዉ እያሰረ እንዳሻዉ እየፈታ የሚያደርግዉን እኩይ ተግባር ፣ ወገኖቻችንን በግፍ በፖለቲካ አመለካከታቸዉ ምክንያት መታሰራቸዉን አጥብቀን እናወግዛለን። ከእሥር ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ሕወሃት/ኢሕአዴግ እንዲፈታ አጠንክረን እንጠይቃለን።

2. ሀገራችን አንድነቷና ሉአላዊነቷ ተከብሮ፤ ሰላምና ፀጥታዋ ተጠብቆ፤ ህዝቧ በነፃነትና በእኩልነት የመኖርና የመሥራት መብት ተከብሮለት፤ የበለፀገች እንድትሆን፤ ገዡው ፓርቲ፤ የፖለቲካ ምህዳሩን ክፍት እንዲያደርግ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

3. የኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት እንዲረጋገጥ፣ ሕግ የበላይ እንዲሆን፣ የዜጎቿ መብት የተረጋገጠባት የዲሞክራሲ ስርዓት የተገነባባትና ጾታ ዘር ኃያማኖት ቋንቋ ሳይባል ሁሉም እኩል የሆኑባት አንዲት ኢትዮጵያን ለመገንባት ትግላችንን እናጠናክራለን።

4. በአገር ዉስጥም የሚኖሩ ሆነ ከአገር ዉጭ የተበተኑ ኢትዮጵያዉያንና የኢትዮጵይ ወዳጆች ሁሉ ከተባበርን መዉጣት የማንችለዉ ተራራ እንደሌላ በማመን ከፊታችን ላለዉ ትልቅ መስዋዕትነት የሚጠይቅ ትዕግስት አስጨራሽ ትግል የዜግነት ድርሻችንን እንደንወጣም በአክብሮት አገራዊ ጥሪ አናቀርባለን።

***<u>ኢትዮጵያ ለዘላለም በነጻነቷና በአንድነቷ ተከብራ ትኑር !</u>***

የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት
የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ - ዲሞክራቲክ
የግንቦት ሰባት ንቅናቄ
የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ማህበራት በሰሜን አሜሪካ
የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ማህበራት በካናዳ
የመላዉ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ድጋፍ ማህበር
ጋሻ ለኢትዮጵያ
የኢትዮጵያ አገራዊ ጉባዔ
የኢትዮጵያ ሶሊዳሪቲ ንቅናቄ